# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የተቋሙ ብቁ ሙያተኞችን የማፍራት ቁርጠኝነት

ጤና ይስጥልኝ ወድ አንባብያን! ባለፈው ሳምንት ጽፁከፋችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፊያ መስመርና ማከፋፋያ ጣቢያዎች ግንባታ ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ክብሮም ካሕሳይ ስለዘርፉ የሥራ ክንውኖች የሰጡንን መረጃ ማቅረባችን ይታወሳል። ለዛሬ ቀጣዩን ክፍል እንደሚከተለው አጠናቅረን እንድታነቡት ጋብዘናችኋል። መልካም ንባብ!

ኢንጂነር ክብሮም እንደሚገልፁት፤ የወደፊቷን ኢትዮጵያ የልማት ዕድል ይወስናል ተብሎ ተስፋ የተጣለው በኤሌክትሪክ ኃይል ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ ለሚከናወኑት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውለው የሀብት ምንጭ የውስጥ አቅም ወይም የውጭ ብድር ሊሆን ይችላል። በፕሮጀክት ትግበራው ሂደት ጨረታን ጨምሮ የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ይሳተፋሉ።

የሥራ ዘርፉ ከከፍተኛ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በየሳምንቱ ፕሮጀክቶችን ይገመግማል። ምን ዓይነት ችግሮች አጋጠሙ? ችግሮችን ለመፍታት ምን ተደረገ? በቀጣይ ሳምንት ምን መሻሻል ይኖርበታል? ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ ችግሮችን እንዴት መቀነስ እንችላለን? መሥራት እየቻልን ሳንሠራቸው የቀሩና ፕሮጀክቱን የሚያጓትቱ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? በሚሉት ጉዳዮች ላይ ግምገማው ያተኩራል። ፕሮጀክቶች ሲጀመሩ በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲጠናቀቁ ውጨዊና ውስጣዊ ችግሮች እየተለዩ አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሰጣቸው ይገልፃሉ።

ዘርፉ በሚያደርጋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የመፈጸም አቅሙን እያሳደገ የመጣ መሆኑን



ኢንጂነር ክብሮም ካሳይ

ሥራ አስፈጻሚው ይናገራሉ። ቀደም ባለው ጊዜ የዘርፉ ዋና ዋና ሥራዎች በአመዛኙ በውጭ ሙያተኞች ይከናወኑ እንደነበር ያስታወሱት ኢንጂነር ክብሮም፤ ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ሥራዎችን በራስ ኃይል ለማከናወን የሚያስችል አቅም እየተገነባ መሆኑን ገልጸዋል። ዘርፉ ከዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ጋር በቅርበት የሚሠራ እንደመሆኑ የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በሚያገኙት ሥልጠና የቴክኖሎጂ፣ የክህሎት እና የእውቀት ሽግግር እያደረጉ አቅማቸውን እንዲገነቡ እድል ይፈጥርላቸዋል።

እንደኢንጂነሩ ገለጻ፤ እስከ አሁን በተደረገው ጥረት እስከ 400 ኪሎ ቮልት የሚደርሱ የማስተላለፊያ መስመሮችን በራስ አቅም የመዘርጋት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በ2014 በጀት ዓመት ብቻ በራስ አቅም በተሠሩ ሥራዎች ለውጭ ሙያተኞች ይከፈል የነበረን አምስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ማዳን ተችሏል።

እንደሥራ አስፈጻሚው አባባል፤ የዘርፉን እድገትና የሥራ ክንውን የሚፈታተኑ ሦስት ጉዳዮች አሉ። የመጀመሪያው የፋይናንስ እጥረት ሲሆን ይህም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁና አገልግሎት በመስጠት ገቢ የሚያመነጩበት ጊዜ እንዲራዘም ስለሚያደርግ ችግሩን ለመቅረፍ መሥራት ይገባል።

ሁለተኛው ከካሳ ክፍያ እና ከስርቆት ጋር የተያያዘ ነው። ካሳ ተከፋዮች በሚያነሷቸው ክርክሮችና አንዳንድ ጊዜም በሚጠይቁት ያልተገባ ክፍያ ምክንያት ፕሮጀክቶች በዕቅዳቸው መሠረት እንዳይሠሩና እንዲጓተቱ ይሆናሉ። በመሆኑም ችግሮቹ በፕሮጀክቶች ላይ የሚፈጥሩትን ጫና ለማቅለል ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የዘርፉን የሥራ እንቅስቃሴ ከሚፈትኑ ጉዳዮች ሌላው ስርቆት ነው። በተለይም በከፍተኛ ወጪ በተተከሉ የብረት ምሰሶዎች ላይ የሚፈጸመው ሥርቆት ተቋሙን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው አገልግሎት እንዳይሰጡ ፈተና እየጋረጠ መሆኑን ገልጸዋል። በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በሚከሰቱ የጸጥታ ችግሮች ምክንያት የሚስተጓጎሉ የግንባታ ሥራዎች መኖራቸውንም አስረድተዋል።

የዘርፉ ግብ በተቋም ውስጥ ብቻ የሚገደብ ሳይሆን እንደ አንድ ተቋራጭ ከተቋሙ ውጭ ባሉ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ለተቋሙ ገቢ ማስገኘት ነው። ዘርፉ በሚቀጥሉት አምስትና ስድስት ዓመታት ከኢትዮጵያ ውጭ ቢያንስ ወደ አፍሪካ ሀገራት ወጥቶ ያካበተውን ልምድ በመጠቀም እየሠራ የውጭ ምንዛሪ የማምጣት ትልም እንዳለው ገልጸዋል። ለዚህም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሰው ሀብት አቅሙን ለማሳደግ መዋዕለ ንዋይ አፍስሶ ብቁ ሙያተኞችን ለማፍራት ጥረት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል። በሀገር ውስጥ ከሚደረገው የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር በተጨማሪ ሠራተኞች ውጭ ሀገር ድረስ እየተላኩ እንዲሰለጥኑ እየተደረገ ነው። ከዚህ ቀደም የሀገር ውስጥ ሙያተኞች ሴራሊዮን ድረስ ሄደው መሥራታቸውን በመጥቀስ አሁንም የተፈጠረው አቅም የማይናቅ እንደሆነ ኢንጂነር ክብሮም አስረድተዋል።

ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ዘርፉ በአፍሪካ ደረጃ ተጠቃሽ የሆነ የኮንስትራክሽን ኩባንያ የመሆን ተስፋ እንዳለውም ገልጸዋል። የዘርፉን አቅም ለማሳደግ በፈረንሳይ የልማት ድርጅት አማካይነት የማማከርና የፋይናንስ ድጋፍ አድራጊነት በቢሾፍቱ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የማሰልጠኛ እና የልህቀት ማዕከል ለመገንባት እንቅስቃሴ መጀመሩን ተናግረዋል። የማዕከሉ ግንባታ ተጠናቆ ሥራ ሲጀምር በሚሰጡ ሥልጠናዎች ተቋሙ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ሙያተኞችን ማፍራት ይችላል። ማዕከሉ የሚያፈራቸው ሙያተኞች ከውጭ ሀገር ባለሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ብቃት እንዲኖራቸው እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

ሕንድ ከዓመታዊ ገቢዋ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በሌላው ዓለም በተሠማሩ ሙያተኞቿ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ እንደሆነ የተናገሩት ኢንጂነር ክብሮም፤ እርሳቸው በሚመሩት የሥራ ዘርፍም ብቁ ሙያተኞችን አፍርቶ በተቀረው ዓለም በማሠማራት የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንደሚቻል ታምኖበት እየተሠራ ነው ይላሉ።

የሥራ ክፍሉ ዕቅድ ግብ እንዲመታ የተቋሙ ሠራተኞችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መረባረብ እንደሚገባቸው ገልጸዋል። በተለይም ከስርቆት እና ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ የሚፈጸሙ ጸያፍ ተግባሮችና ሳንካዎች የተቋሙን አቅም የሚያሽመደምዱና ያሰበበት ደረጃ ላይ በፍጥነት እንዳይደርስ የሚያደርጉ በመሆናቸው ተቋሙ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ችግሮችን በጋራ የመፍታት ባሕሉን ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን የተናገሩት ሥራ አስፈጻሚው፤ በቀጣይም ተቋሙ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ሁሉም ተባባሪ እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል